# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከሜይ 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ከሜይ 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሜይ 2023
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከሜይ 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ..... 3

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ..... 5

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10 /2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ..... 6

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10 /2023 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ..... 7

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ..... 7

እ.ኤ.አ ከሜይ 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... 8

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... 8

እ.ኤ.አ ከሜይ 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... 9

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ..... 9

እ.ኤ.አ ከሜይ 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ..... 10

ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከሜይ 11-20, 2023 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲ.ሴ ..... 10

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሜይ 11-20, 2023 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ. ..... 10

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሜይ 11-20, 2023 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ. ..... 10

እ.ኤ.አ ከሜይ 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... 11

እ.ኤ.አ ከሜይ 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ..... 11

# እ.ኤ.አ ከሜይ 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ


በሜይ የመጀመርያ አስር ቀናት የበልግ ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ገጽታዎች አንፃራዊ በሆነ መልኩ ተጠናክረው ተስተውለዋል፡፡ በመሆኑም የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት ነበራቸው፡፡ በዚህም መሠረት በአስሩ ቀናት ውስጥ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የተስፋፋ ዝናብ ያገኙ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ደግሞ ከ30 ሚ.ሜ የበለጠ ከባድ ዝናብ ነበራቸው። ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአርባ ምንጭ 43.8፣ በኮምቦልቻ 43.0፣ በአቦቦ 30.2፣ በአምባ ማሪያም 61.4፣ በአምደ ወርቅ 34.4፣ በአርጆ 37.9፣ በባቲ 50.0፣ በጭፍራ 50.2፣ በዲላ 49.5፣48.4፣ በኢጃጂ 65.2፣ በጊምቢ 33.9፣በጉንዶ መስቀል 47.7፣ በቡሌሆራ 100.6፣ በጅግጅጋ 38.8፣ በአይከል 41.5፣ በቡርጂ 33.4፣ በጃራ 33.8፣ በኮንሶ 54.6፣ በሰዉላ 40.8 እና 78.8፣ እንዲሁም በተርጫ 37.8 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

በሌላ በኩል የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በሀገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች ላይ ማለትም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ ዳርቻዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ35 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ከ35 ዲ.ሴ በላይ የተመዘገበባቸውን ሥፍራዎች ለመጥቀስም ያህል በአርባ ምንጭ 38.6፣ በጎዴ 37.4፣ 37.6፣ 38.2፣38.6፣ 38.8፣ 39.1፣ መተሃራ 35.6፣ በአቦቦ 35.0፣ 35.2 እና 39.6፣ በአዋሽ አርባ 35.0፣ 36.0፣ 36.5 እና 38.0 በአይሻ 38.5 እና 39.5፣ በዳሊፋጊ 35.2፣ 36.0 እና 37.0፣ በፉኚዶ 35.0፣ 35.5 እና 36.0፣ በጋምቤላ 35.8፣ 37.4 እና 39.6፣ በገዋኔ 35.0፣ 5.4፣ 36.4 እና 37.4 በላሬ 36.2፣ 38.0 38.2፣ በአሊያ 35.4፣በሚሌ 37.0፣38.5፣39.5፣ በፓዌ 36.4፣36.8፣ በሰመራ 36.0፣ 36.4፣ 38.0 እና 39.0፣ በፅፅቃ 35.8፣ 36.4፣ 37.8 እና 38.8 ዲ.ሴ ሲሆን፤ በተጨማሪም በጥቂት አከባቢዎች ላይ ደግሞ ከ40 ዲ.ሴ በላይ ተመዝግቧል፡፡ ለአብነትም በአይሻ 40.0 እና 40.5፣ በዱብቲ 40.0፣ 41.0፣ 41.5 እና 42.0፣ በጋምቤላ 40.0፣ በመተማ 40.0፣ 40.6፣ 41.0፣ 41.2፣ 41.4 እና 41.6፣ በሚሌ 40.0 እንዲሁም በሰመራ 40.2 እና 40.4 ዲ.ሴ የደረሰ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን እንደተመዘገበ ከየጣቢያዎቹ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ ዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከምዕራብ ጎንደር፣ ከምዕራብ አሶሳና መተከል እንዲሁም ከሶማሌ ክልል ከዶአሎ፣ ከቆራሄና ከሸበል ዞኖች በስተቀር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከ5-177 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ 2-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፀፀር ከአፋር ዞን 5 እና 3፤ ከአማራ የዋግህምራ፣ የሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ የደቡብ ጎንደር፣ የምስራቅና ምዕራብ ጎጃምና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ አኙዋክ ዞን፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፤ አብዛኛው የኦሮሚያ ክልል ዞኖች፤ ከሶማሌ የጃረርና የኤረር ዞኖች እንዲሁም ሀረሪና አዲስ አበባ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10 /2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2    ኢ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10 /2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10 /2023 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከሜይ 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የመጀመሪያዎቹ የሜይ አስር ቀናት በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የተስፋፋ ዝናብ ያገኙ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ተዘርተው ፍሬ በማፍራት እና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች ቀጣይ እድገታቸው ላይ የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሰብሎች ለዘር እርሻ እንቅስቃሴ፣ ለቋሚ ሰብሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት በተጨማሪም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳር እና ለመጠጥ ዉሃ አቅርቦት አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ የነበረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ለአብዛኛው የእርሻ እንቅስቃሴ በተለይም በአዎንታዊ መልኩ ውኃን ለመሰብሰብና ለማጠራቀም ጥሩ ሁኔታ የፈጠረ ቢሆንም፣ ባስከተለዉ የጎርፍ መከሰትና የመሬት መንሸራተት አንዳንድ አካባቢዎች ላይ በንብረትና በህይዎት እንዲሁም በግብርናዉ እንቅስቃሴ ላይ በተወሰነ መልኩ አሉታዊ ተፅእኖ ነበረዉ (ካርታ 4) ፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከሜይ 1-10/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳልፍነው የሜይ የመጀመርያው አስር ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ ነበር፡፡ ከእነዚህም መካከል በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ ኦጋዴን፣ የላይኛውና የመካከለኛው አባይ፣ አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው፡፡ በተጨማሪም በኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ እና በአባይ ጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከሜይ 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ


በመደበኛ ሁኔታ በሜይ ሁለተኛው አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ቀስ በቀስ ከሰሜን ምሥራቅ ላይ እየቀነሰ ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ ይሄዳል:: በተጨማሪም በደቡብ ኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በደቡብ አጋማሽ ላይ ቀጣይነት እንደሚኖራቸውና በተመሳሳይ ሁኔታም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከቀን ወደቀን በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች እንደሚጠናከር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።


በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ የምዕራብና የምሥራቅ ሐረርጌ፣ አርሲና ባሌ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን ሸዋ እንዲሁም የባህር ዳር ዙሪያ፤ ከትግራይ ክልል በጥቂት የምዕራብ፣ የምስራቅና የደቡብ ዞኖች፤የጋምቤላና የቤንሻንጉል ክልል ዞኖች ፣አዲስ አበባ፣ድሬዳዋ፤ ሐረሪ ክልል፤ አብዛኛው የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ የሲዳማ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤ ከሶማሌ ክልል ፋፈን እና ጃራር ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና አልፎ አልፎም በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚያገኙ ሲሆን በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይም ከባድ ዝናብ እንደሚኖር የአህዛዊ ትንበያ መረጃ ያመላክታል።በአንጻሩ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፤ ከአፋር ክልል ዞን 3 እና 5፤ከኦሮሚያ ክልል ቦረና እና ጉጂ ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ሳሳ ካለ የደመና ሽፋን ጋር ተያይዞ ደረቃማ ቀናት እያመዘነባቸው በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ስፍራዎች ግን ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሜይ 11-20, 2023 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሜይ 11-20, 2023 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከሜይ 11-20, 2023 የሚኖረዉ የቀኑ ከፍተኛ የአየር ሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## ኢ.ኤ.አ ከሜይ 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የሜይ ሁለተኛው አስር ቀናት የእርጥበት ሁኔታው ከሰሜንና ከምስራቅ የበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየቀነሰ በአንፃሩ በደቡብ አካባቢዎች ላይ የመቀጠል አዝማሚያ ሲኖረው፤ በምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ግን እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው፡፡

በሚቀጥለው የሜይ ሁለተኛዉ አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በደቡብ አጋማሽ ላይ ቀጣይነት እንደሚኖራቸውና በተመሳሳይ ሁኔታም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከቀን ወደቀን በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እንደሚጠናከር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህም ሁኔታ ከላይ በትንበያው በተጠቀሱት አካባቢዎች የሚገኘው እርጥበት በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚገኙ የግጦሽና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ እንደሚሄድ የሚጠበቀው እርጥበት በተለይም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራትና አስፈላጊ ዝግጅት ለማድረግ መልካም አጋጣሚ እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖራቸው ስለሚችል ቅፅበታዊ ጎርፍን ከመከላከል ጎን ለጎን የውኃ ማቀብ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ስለሚሆን፤ የሚመለከታቸው አካላት ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡

## ኢ.ኤ.አ ከሜይ 11-20/2023 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የሜይ ሁለተኛ አስር ቀናት በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በመካከለኛው በሚገኙ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አብዛኛው ባሮአኮቦ፣ አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ ተከዜ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌ እና አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በሚኖረው ከፍተኛ እርጥበት ለጎርፍ ተጠቂ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ቅድመ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም መካከለኛው አዋሽ፣ ገናሌ ዳዋ እና በጥቂት አፋር ደናክል እና ኦጋዴን ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት ሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡